## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# ሚያዚያ 23 (ሜይ ዴይ)
# ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን ሲዘከር

ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም.

የዘንድሮው ሚያዚያ 23 2002 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን የሚከበረው/የሚታሰበው የላብ አደሩ ፍላጎት ያልተጠየቀበትና ያልተካተተበት የሠራተኛ ሕግ በጫንቃቸው ላይ ተጭኖ እየተበደሉ ባሉበት፤ ለኑሯቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ዋጋቸው በናሩበት፤ የሥራ አጡ ቁጥር እየጨመረ በሚሄድበትና ሥራ ካላቸውም ቢሆኑ በርካታዎች የሚያገኙት የሥራ ክፍያ በየጊዜው እየናረ ካለው የዕቃና አገልግሎት ዋጋ መመጣጠን ባልቻሉበት፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የዋጋ ግሸበት ተደምሮበት ከድህነት ወለል በታች ለመኖር ተገደውና ለመንገድ አዳሪነት ተዳርገው ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ተላላፊና ቀሳፊ በሽታዎች በቁጥጥር ሥር ሊውሉ ቀርቶ እየተስፋፉ በሚገኙበት፤ ረሃብና ችግር በእያንዳንዱ ቤት ደባል ኗሪ ሆነው በሚገኙበትና ዛሬም ከ6 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎቻችን የባዕዳን ምጽዋት ለጋሾች ጥገኛ ከመሆን ባልተላቀቁበት፤ አገዛዙም ሆነ አሠሪዎችና ቀጣሪዎች በብጣሽ ወረቀት ሠራተኞችን የማባረር ባለመብት በሆኑበት ወቅት በመሆኑ በአሉን ልዩ አድርጎታል።

ይህ የሠራተኞች ቀን በዛሬው ዕለት ሲዘከር፣ ለዚህ ቀን መከበርና ሠራተኛው የተለያዩ መብቶቹና ጥቅሞቹ እንዲከበሩለት ያደረጋቸው ተጋድሎዎችና የከፈላቸው የሕይወት ዋጋዎች በሁሉም ሀገር በላብ አደሩና በሠራተኛው የታሪክ መዝገብ ተጽፈው ለወደፊቱ ትውልድ የተመከሮ እውቀት መገብያ ዋና መሠረት አድርጎ እንዲዘከራቸው ብቻ ሳይሆን ገና መፍትሄ ያላገኙ የፖለቲካ፤ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ እንዲያገኙ ቆርጦ ለመታገል ቃል ኪዳኑን ለማደስም ጭምር ነው።

በሀገራችንም ቢሆን ነጻነቱ የተጠበቀ፣ በራሳቸው ሙሉ ኃላፊነት የሚተዳደርና የራሳቸው የሆነ የሚታገሉበት ድርጅታቸውን ለመመስረት ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች መቼም ቢሆን የሚረሱ አይደሉም። እነደነአበራ ገሙ፣ ማርቆስ ሀጎስ፣ ዳሮ ነጋሽና ሌሎችም በርካቶች ለሠራተኛው መብት፣ መከበር ሲሉ የሕይወት ዋጋ የከፈሉትን በዚሁ ቀን ከልብ የምንዘከራቸው ናቸው። በሕይወት ዘመናችን ካየናቸው ሦስት አገዛዞች በተለይም የደርግና የወያኔው ለሠራተኛው መብትና ጥቅም የቆሙ እየመሰሉ ግና ሲበድሉት፤ መብቱን እየተጋፉ ሲበዘብዙት፤ ጠንካራ የሆኑ መሪዎቻቸውንና አባሎቻቸውን እያሰሩ እንግልት እያደረሱ ለሞት፤ ለአካልና ለመንፈስ ስብራት ዳርገው፤ የብዙዎቹንም ደብዛ አጥፍተዋል። ነጻ ማህበሮቻቸውን በተለጣፊዎች እንዲነጠቁ አድርገው ድርጅት አልባ አድርገዋቸዋል። ከባዕዳን ቀጣሪዎች ጋር በመመሳጠር ሠራተኛውን መብት አልባ በማድረግ በደል እንዲፈጸምባቸው ተባብረዋል። የወንጂና

የመተሃራ ፋብሪካ ሠራተኞች ላይ የደረሰው ጉዳት ቅሪቱ ከነሱ አልፎ በወለዷቸው ልጆች ደርሶ ከማህበራዊ ኑሮ እንዲገለሉ ተዳርገዋል። በወያኔ አገዛዝም ቢሆን የቻይና ቀጣሪዎች ሠራተኛውን እንዳሻቸው እንዲያደርጉት የፈቀደ በመሆኑ ሠራተኞቹ አቤት የሚሉበትና ፍትህ የሚያገኙበት፤ የደረሰባቸው በደሎች እንዳይደገሙ ደጀን የሚሆንና ባጠቃላይ ምንም ዓይነት ዋስትና አጥተው ለቀጣሪዎቻቸው የግል አገልጋይ መዳረጋቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በሀገራችን የሚገኙትን ኩባኒያዎችንና ኢንዱስትሪዎችን ሙሉ በሙሉ በራሱ ፖለቲካ ሥር አድርጎ ሠራተኛውን እያንገላታ ያለው ወያኔ መደባዊ አንድነቱን እንዳያረጋግጥና እንዳያጠናክር በብሔረሰብ ከመከፋፈሉ ባሻገር፡ በመዋቅር ማስተካከያ ሳቢያ በርካታ የፋብሪካና የኩባንያ ሠራተኞችን ያለምንም የኑሮ ዋስታና ሜዳ ላይ በመወርወር ያደረሰባቸው በደልና ጥፋት አስከፊነቱና አሳዛኝነቱ ለነጋሪም የሚያሳፍር ነው። ለተለያዩ በደሎች እያጋለጣቸውና በፊት የነበሩትንም በቀጣይነት እንዲኖሩ እያደረገ ያለው ወያኔ ኢትዮጵያን በዴሞክራሲ ጎዳና እንድትጓዝ አድርጊያለሁ፤ ዘንድሮም እንዳለፉት ተከታታይ ዓመታት ሁሉ አሥር በመቶ የኤኮኖሚ እድገት አስገኝቻለሁ፤ ሠራተኛውን ከብዝበዛ እንዲላቀቅ አስተዋፅዖ አበርክቻለሁ በማለት በውሸት በተሞላ ፕሮፓጋንዳና በተለጣፊዎቹ አማካኝነት መግለጫ በማስወጣት እራሱን ማሞገሱና ማስሞገሱ የማይቀር ቢሆንም እስከዛሬም ሞክሮ የከሸፈበት ነውና አሁንም በመሬት ያለውን ተጨባጭ ዕውነታ ሊቀይረው ስለማይችል፤ ውድቅ ሊሆን እንደሚችል ምንም ዓይነት ጥርጥር የለንም።

በቅርብ ጊዜ በግንቦት 2002 ዓ.ም. እንዲጠናቀቅ ለታሰበው ምርጫ ተብዬ ትዕይንት ወያኔ የራሱን አገዛዝ ለማስቀጠል የሚያስችለው ዝግጅቱን ከመጨረሱም በተጨማሪ በውይይቱ የተደረጉትን የሃሳብና የአቋም ገለጻዎችን ላዳመጠ፣ ወያኔ በውሸት የተካነና ወደፊትም በሕዝባዊ ትግል ከሥልጣን እስካልተወገደ ድረስ በዚሁ ሽምጠጣው የሚቀጥልበት ለመሆኑ በገሃድ አረጋግጧል። በመሆኑም ወያኔን ለሚቀጥለው አምስት አመት ሕዝባችንን እንዲገዛ እውቅናና ይሁንታ ሊያስገኝለት በሚችለው ቲያትር ተካፋይ መሆኑ ከጥቅሙ ጉዳቱ ከፍተኛ ነውና የድምጽ ተአቅቦ ማድረጉ ተገቢም ነው ብለን እናምናለን። ባለፈው በተደረገው ሕዝባዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹን በሚያስገርምና በሚያስደንቅ ሁኔታ ነፍጎት ከሥልጣን ቢያስወግደውም ከ200 በላይ የሚሆኑ ዜጎቻችንን በአግዓዚ ጦሩ አማካኝነት ገሎ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ደግሞ በማሳፈስ ለእስርና ለዱር አራዊት ሰለባነት ዳርጎ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ የጥፋት ተልዕኮውን ከግብ ለማድረስ አምባገነናዊ ሥርዓቱን ያሰፈነ ሕገ ወጥ ቡድን ነው።

ይህ ከሌሎች ኢሰብዓዊነት ከተጠናወታቸው ድርጊቶቹ ጋር ተደምሮ በፍጹም ይቅርታ ሊደረግለት የሚገባ አይደለም። ካለፉት ጥቂት ወራት ጀምሮ ይህንኑ ሕገ ወጥነቱንና የጥፋት ተልዕኮውን ለመሸፈን



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ያላከናወናቸውን አድርጊያለሁ እያለ ለወደፊትም ያቀዳቸውን እቅዶቹን በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ እያጀበ በሞኖፖል በያዛቸው የዜና ተቋማት እያስለፈለፈ ይገኛል። በዚህ ደግሞ ያለፉት ኃጢአታዊ ድርጊቶቹን ሊፍቅ፤ የተካነበትን አምባገነንትም ሊሸፍን አይቻለውም። በአሁኑ ጊዜ በዚህ እልህ አስጨራሽ ትግል ላብ አደሩና ሠራተኛው ግምባር ቀደም ሚና እየተጫወቱ ናቸውና በዛሬው የዓለም አቀፍ ሠራተኞች ቀን ይህንን ሚናቸውን ይበልጥ የሚያጎለብቱበት ታክቲክና ዘዴ በመቀየስ የሚዘከሩት ይሆናል።

ኢሕአፓ በዚህ ተልዕኳቸው ከላብአደሩና ከሠራተኛው ጎን በመሆን ይህንን ቀን አብሮ ሲዘክር ከልቡ ነውና ያልተመለሱ ጥያቄዎቻቸው መፍትሄ እንዲያገኙ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ሙሉ ድጋፉን እየሰጠና የገባውንም ቃል ኪዳን እያደሰ ለእውነተኛ መሪዎቹና ቆራጥ አባላቱ ያለውን አድናቆትና ከበሬታም በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል። ወያኔ የጫነባቸውን የክፍፍል ዘይቤ አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት ሁኔታ በማክሸፍና የትግል አንድነታቸውን በማጠናከር ትግላቸውን እንዲቀጥሉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያስተላልፍላቸዋል።

የላባአደሩና የሠራተኛው ትግል ይለምልም !!
በተባበረ ትግል እናቸንፋለን !!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France